# የማኅበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት አደረጃጀትና አመራር መመሪያ ቁጥር 84/2013

## CLC Impelemenatation Guide Line

ረቂቅ ጽሑፍ

**ትምህርት ሚኒስቴር**

**አዲስ አበባ**

2008 ዓ.ም

ማውጫ ገጽ


| | | |
|---|---|---|
| | መግቢያ------------------------------------------------------------ | 2 |
| 1.1 | የመመሪያው አስፈላጊነት------------------------------------------------ | 3 |
| 1.2 | የመመሪያው አላማ---------------------------------------------------- | 3 |
| 1.3 | በመመሪያው ውስጥ የተካተቱ ቃላት ትርጓሜዎች--------------------------------- | 4 |
| 1.4 | የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ምንነት፡------------------------------------ | 4 |
| 1.5 | የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ፋይዳ፡------------------------------------- | 5 |
| 1.6 | የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ዓላማ---------------------------------------- | 5 |
| | 1.6.1 አጠቃላይ ዓላማ------------------------------------------------- | 5 |
| | 1.6.2 ዝርዝር ዓላማ-------------------------------------------------- | 5 |
| 1.7 | የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ዋናዋና መርሆዎች፡------------------------------ | 6 |
| 1.8 | የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከል ምስረታ------------------------------------------ | 6 |
| | 1.8.1 የመማማሪያ ማዕከላቱ ቤት/ቦታ-------------------------------------- | 7 |
| | 1.8.2 የሰዉ ሀይል-------------------------------------------------- | 8 |
| | 1.8.3 የቁሳቁስ ሀብት ምደባ-------------------------------------------- | 8 |
| 1.9 | በማህበረሰብ መማማሪያ ማዓከላት የሚሰጡ አገልግሎቶች/ ---------------------------- | 9 |
| 1.10. | የማህበረሰብመማማሪያማዕከላት(CLC)ተሳታፊዎች/ተጠቀሚዎች----------------------- | 12 |
| 1.11. | የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት አደረጃጀትና አመራር------------------------- | 13 |
| | 1.12.1 የፌደራል ቦርድ አባላት ተግባርና ኃላፊነት---------------------------- | 13 |
| | 1.12.2 የፌደራል ቴክኒክ ካሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነት------------------------ | 14 |
| | 1.12.3 የክልል/ የከተማ አስተዳደር ቦርድ አባላት ተግባርና ኃላፊነት------------ | 15 |
| | 1.12.4 የክልል/ የከተማ አስተዳደር ቴክኒክ ካሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነት---- | 16 |
| | 1.12.5 የዞን/ ወረዳ ቦርድ አባላት ተግባርና ኃላፊነት---------------------------- | 16 |
| | 1.12.6 የዞን/ ወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላትተግባርና ኃላፊነት---------------------- | 17 |
| | 1.12.7 የቀበሌውየጎልማሶች ትምህርት ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት------------------ | 18 |
| | 1.12.8 የማኅበረሰቡ ተግባርና ኃላፊነት------------------------------------- | 19 |
| 1.13 | በማህበረሰብተሳትፎ፣ባለቤተነትና የማዕከላቱቀጣይነትንማረጋገጥ፣-------------- | 20 |
| 1.14 | ለማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላትሀብት መመደብና ማሰባሰብ------------------- | 21 |
| | 1.14.1 ከመንግሥት ለማዕከላቱ የሚመደብ በጀት------------------------------ | 21 |
| | 1.14.2 ከተላያዩ ለጋሽ አገራት የሚመደብ------------------------------------ | 21 |
| | 1.14.3 የሀብት ማሰባሰቢያ ዘዴዎች--------------------------------------- | 22 |
| 1.15 | የማህበረሰብመማማሪያ ማዕከልክትትልናግምገማ-------------------------------- | 22 |
| | 1.15.1 የክትትልና ግምገማ ዓላማ | 22 |
| | 1.15.2 የክትትልና ግምግማ ሚና------------------------------------------- | 22 |
| | 1.15.3 በክትትልና ግምገማ ሂደት የሚደረግባቸው ነጥቦች-------------------------- | 23 |
| 1.16 | ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች-------------------------------------------- | 23 |

## መግቢያ

ትምህርት ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ዕድገት ዋና መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም ሀገሮች ዜጎቻቸው የትምህርት እድል እንዲያገኙ የተለያዩ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን ቀርጸው በሚፈልጉት የትምህርት አማራጮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡ለዚህም የተለያዩ የትምህርት አቅርቦት ስልቶችን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ከሚያስችሉን የትምህርት አቅርቦት ፕሮግራሞች መካከል አንዱ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ከመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም በተጨማሪ መደበኛ ባልሆነው የትምህርት ፕሮግራም ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ የሆኑና በተለያዩ አጋጣሚ የትምህርት ዕድል ያላገኙ በርካታ ወጣቶችና ጎልማሶችን የትምህርት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተለማጭ/flexible/ የሆነና እና ከተሳታፊው የዕለት- ተዕለት ስራ /ክንውን ጋር ተቀናጅቶ የሚሠጠው፣ በህብረተሰቡ ተሳትፎ ተግባራዊ የሚሆን፣ ችግር ፈቺ፣ ቁልፍና ኑሮን አሻሻይ በሆኑ ክህሎቶች ላይ ባተኮረ የንባብ፣ የጹሁፍና የስሌት ክህሎት ጋር ተቆራኝቶ የሚሰጥበት የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም አንዱ ነው፡፡ በአገራችን የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተዘርግቶ ትምህርቱ መሰጠት ከተጀመረ አምስት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ በ2ኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድም የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ፕሮግራም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ቀደምሲል በጎልማሶች ትምህርት የተሳተፉም ሆነ ያልተሳተፉ ጎልማሶችና ሌሎች የአካባቢ ማህበረሰብ አባላት በአካባቢያቸው በሚገኙ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ተሳታፊ በመሆን ፍላጎታቸውን ያገናዘበ የማንበብ፣ የመጻፍ የማስላትና የተግባቦት ክህሎት የሚቀስሙበትና የሚያዳብሩበት ፣ ከዕለት ተዕለት ኑሯቸው ጋር የተዛመደ የሙያ ስልጠና ወስደው ወደ ተግባር የሚገቡበትና የተለያዩ የመዝናኛ አገልግሎት የሚያገኙበት የዕድሜ ልክ ትምህርት ለማስቀጠል የሚያስችል የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት (Community Learning Center) ማቋቋም አስፈላጊ ሆኗል፡፡ በመሆኑም ማዕከላቱን ለማቋቋም፣ ለማደራጀትና ለመምራት የሚያስችል የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት (CLC) አደረጃጀትና አመራር መመሪያ ከዚህ በታች ተዘጋጅቶ ቀርቧል ፡፡

### 1.1. ***የመመሪያው አስፈላጊነት***

*ሀገራችን የተያያዘችውን የህዳሴ ጉዞ ለማፋጠንና ቀደምሲል በተከታታይ የተመዘገበውን ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት ቀጣጥነት እንዲኖረው ለማድረግ መንግስት ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል ፡፡ በተለይም በምርት ስራ ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ የሆነውን ጎልማሳው የህብረተሰብ ክፍል ከዕለት ተዕለት ህይወቱ ጋር የተዛመደ፣ የተለያየ ይዘት ያለውና በተለያዩ አካላት በቅንጅት የሚተገበር ፣ ለተሳታፊ ጎልማሶች ወቅታዊ ምላሽ የሚሰጥ፣በጎልማሶች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ፣ የተሻሻለና አዲስ ዓይነት አሰራርን በማስተዋወቅ የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የሚረዳ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በተለይም በአንደኛ የእድገትና ትራንስፎሜሽን የዕቅድ ዘመን* 8 *ሚሊዮን ጎልማሶች የሁለት ዓመቱንየተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትፕሮግራም ያጠናቀቁ ቢሆንም የታቀደውን ዕቅድ ማሳካት አልተቻለም፡፡*

*ጎልማሳው ህብረተሰብ ክፍል አመለካከቱ ክህሎቱ ዳብሮ በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፓለቲካዊ ያለው ተሳትፎው የላቀ እንዲሆንና የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ዕድገትማፋጠን እንዲቻል በ*2*ኛው የእድገትና ትራንስፎሜሽን እቅድ ለጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ የትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የተለያዩ ዕቅዶችም ታቅደው እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት ሀገራችን በ*2017 *ዓ.ም ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ የተጣለውን ግብ ከዳር ለማድረስ በጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት አካል የሆነውን የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት* (CLC) *በማቋቋምቀደምሲል በጎልማሶች ትምህርት የተሳተፉም ሆነ ሌሎች የአካባቢ ማህበረሰብ አባላት በማሳተፍ የዕድሜ ልክ ትምህርትን ማስቀጠል ይገባል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል ይህ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት* (CLC) *አደረጃጀትና አመራር መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡*

### 1.2. ***የመመሪያውዓላማ***

- ❖ *ለማህበረሰቡ የተለያዩ የትምህርት አማራጮችን በማቅረብ የዕድሜ ልክ ትምህርት ለማስቀጠል የሚያስችል የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት* (CLC) *እንዲቋቋሙ ለማድረግ፣*
- ❖ *የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት* (CLC) *አደረጃጀት፣ አመራርና አሰራር ስርአት እንዲዘረጋ ለማድረግ፣*

- በማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከል የሚሰጡ አገልግሎቶች ጥራታቸው የጠበቁ እንዲሆኑ ለማድረግ፣

## 1.3 በመመሪያውውስጥየተካተቱቃላትትርጓሜዎች

Formatted: Indent: Left: 1", No bullets or numbering

- **የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት(CLC)፡-** ማለት የአካባቢው ማህበረሰብ አባላት ፍላጎታቸውን ያገናዘበ የማንበብ፣ የመጻፍ የማስላትና የተግባቦት ክህሎት የሚቀስሙበትና የሚያዳብሩበት ፣ ክዕለት ተዕለት ኑሯቸው ጋር የተዛመደ የሙያ ስልጠናና የተለያዩ የመዝናኛ አገልግሎት የሚያገኙበት መማማሪያ ማዕከል ማለት ነው፡፡
- **ጎልማሶች፡**ማለትዕድሜያቸው 15-60 ዓመት የሆኑ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተጠቃሚዎችን የሚመለከትነው፡፡
- **የእድሜ ልክት ትምህርት ማለት፡-**የዕድሜ ልክ ትምህርት የምንለው መደበኛ ትምህርት (Formal Education)፣ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት (Non- Formal Education) እና ኢ-መደበኛ ትምህርትን ( Informal Learning) ሁሉ የሚያካትት ሲሆን ዜጎች በህይወት ዘመናቸው ሁሉ በራስ ተነሳሽነት ጭምር የሚማማሩበትና ዕውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውንና አመለካከታቸውን በማሻሻል የግል ብቃታቸውን በማሳደግ ኑሮአቸውን የሚያሻሽሉበትና ለአገር ዕድገትም ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት ትምህርት ማለት ነው፡፡
- የሙያ ሥልጠና፣

## 1.4የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ምንነት፡-

የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከል መደበኛ ያልሆነ ተከታታይ የጎልማሶች ትምህርት ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት በተወሰነ ደረጃ የሚችሉ፣ የሁለት ዓመቱን የጎልማሶች ትምህርት ያጠናቀቁ፣ የመደበኛ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአጭሩ ያቋረጡ፣ ምንም ዓይነት ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ዜጎችመሠረታዊ የማንበብ ፣ የመጻፍና የማስላት ክህሎታቸው የሚያገኙበትትበተለያዩ የልማት ጉዳዮች ላይ አጫጭር የህይወት ክህሎትና የሙያ ስልጠናየሚቀስሙበትና የተለያዩ ውድድሮችን በማካሄድ በመዝናናት የሚማማሩበትማዕከል ነው፡፡ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የማህበረሰቡን ፍላጎት ባማከለ መልኩ የተለያዩ የልማት ተግባራትየሚከናወኑባቸው ስፍራዎች ናቸው

## 1.5የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ፋይዳ፡-

- የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ለማምጣት የማኅበረሰብ የንቅናቄ መፍጠሪያ ማዕከላት በመሆን ያገለግላሉ

- የአካባቢው ማህበረሰብ ተቋም  በመሆን የማህበረሰቡን  ባህላዊና ዘመናዊ እውቀት በማጎልበትና በማሳደግ ድህነትን በማስወገድ ዜጎች የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ኢኮኖሚ እንዲያሳድጉ፣ንቃተ ህሊናቸውን እንዲያዳብሩና የተሻለ የአኗኗ ዘይቤ  እንዲኖራቸው ያደርጋሉ ፣
- የተሳታፊ ጎልማሶችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የልማት ጉዳዮችን ለማሳካት አጫጭር የስልጠና መስጫ ማዕከላት በመሆን ይገለገሉባቸዋል፣
- ተሳታፊ ጎልማሶች ተከታታይነት ባለው መልኩ ተማምረው ባገኙት ዕውቀትና ክህሎት ተጠቅመውበገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሳተፉና ገቢያቸውን እንዲያሳድጉ፣ጤናቸውንና አካባቢያቸውን በመጠበቅ ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲያሻሽሉ ያደርጋሉ፣
- ተሳታፊ ጎልማሶችበተሻለ ሁኔታ እራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ በማድረግ ቀጣይነት ያለው እድገት በአካባቢያቸው እንዲፈጥሩ ያስችላቸዋል፣
- የተለያየ ይዘት ያላቸው ርዕሶች በአንድ ማዕከል ተደራጅተው የሚቀርቡበት በመሆኑ ሁሉም የአካባቢው  ማህበረሰብ አኗኗሩ የተሸሻለ እንዲሆን፣ ኢኮኖሚውን የሚያሳድግበትና ሁለንተናዊ ዕድገት እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡

### 1.6የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ዓላማ፡-

#### 1.6.1 አጠቃላይ ዓላማ

የተከታታይ ትምህርትና ስልጠና መስጫ ማዕከል በመሆን የኅብረተሰብን የእድሜ ልክ ትምህርት በትምህርት፣ በስልጠና በመረጃ አገልግሎት ምሉኡ በማደረግ የግለሰብን፣ የማኅበረሰብና የሀገርን እድገት ለማፋጠን

#### 1.6.2 ዝርዝር ዓላማ

- የጎልማሶችን የማንበብ፣መጻፍና የማስላት ክህሎትማበልጸጊያ ማዕከላት እንዲሆኑ ማስቻል፣
- የማኅበረሰብ አባላትን አቅማቸውን በማሳድግ ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲኖር ማዕከላቱን ባግባቡ ማደራጀት፣
- የተሻለ አኗኗር  ለመኖር የመረጃ ልውውጥና የአገልግሎት አሰጣጥን ማሳደጊያ ማዕከላት እንዲሆኑ ማስቻል፣
- ዜጎች በአካባቢያቸው ስለሚገኙ ሀብቶች በቂ ግንዛቤ እንደኖራቸውና በአግባቡ እንዲጠቀሙ  ማድረግ፣

- ዜጎች ስለመብታቸውና ግዴታቸው የሚያውቁባቸው ማዕከላት እንዲሆኑ ማስቻል፣
- የተለያዩ የሙያ ክህሎት፣ስልጠና የሚሰጥባቸው ማዕከላት በመሆን የማኅበረሰብን እድገት ማፋጠን፣
- የማኅበረሰብን የቁጠባና ብድርባህል ማበልጸጊያ ማዕከላት እንዲሆኑ ማገዝ፣
- የአካባቢው ማህበረሰብ በውይይት ግጭትን የሚፈታባቸው ማዕከላት እንዲሆኑ ማስቻል፣
- የአካባቢው ማህበረሰብባህላዊ እሴቶችን መገለጫ ክብረበዓል የሚከበርባቸውና የመዝናኛ ማዕከላት እንዲሆኑ ማድረግ
- የአካባቢው መንግስትና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች የሚያከናውናቸውን የተለያዩ የማህበረሰብ ልማት እንቅስቃሴዎችን ማፋጠኛ ማዕከላት እንዲሆኑ ማስቻል።

## 1.7የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ዋናዋና መርሆዎች፡-

- የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት የማህበረሰቡ የሆኑ ፣ በማህበረሰቡ የሚመሩና ለማህበረሰቡ ጥቅም የሚሰጡ፣
- የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ለሁሉም ዜጋ በአካባቢው ማህበረሰብ ፍላጎትና ንቁ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ፣ እንዲሁም ለማህበረሰቡ የመረጃ ምንጭና የአቅም ማጎልበቻ ጣቢያ በመሆን አንዱን አካባቢ ከሌላው ጋር የሚያገናኙ፣
- የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላትአመቻቾች በኃላፊነት የሚያስተዳድሩትና የእድሜ ልክ ትምህርት የሚከናወንባቸው ፣
- የማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ሁሉም የማህበረሰብ አባላት የሚያሳትፍ፣

## 1.8የማኅበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ምስረታ

የማህበረሰብ መማማሪያ መአከላት መፈጠር አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደልም በመሆኑምኅብረተሰቡ የጋራ ጉዳዮቹን በጋራ ለማየት ያቋቋማቸው ማኅበራት እንደመነሻነት ተወስደዋል የሚለውን ሀሳብ ብዙዎች ይስማመበታል። የማኅበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት በአንድ አካባቢ የሚገኙ ጎልማሶች የእድሜ ልክ ትምህርት የሚያገኙባቸው ተቋማት ሲሆኑ ለማኅበረሰቡ ዕድገት፣ መለወጥና የኑሮ መሻሻል ትልቅ ፋይዳ አላቸው። የነዚህ የመማማሪያ መዕከላት አጠቃላይ ገፅታና ሁለገብነት እንደአገሮች ፍላጎትና የኢኮኖሚ አቅም የሚወሰን የሆናል። ከዚህ አኳያ በአገራችን በዋናነት ለሚሰጠው የ የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ

ትምህርት ፕሮግራሞችበማዕከልነት የሚያገለግሉ ለማኅበረሰብ በሚያመች ሁኔታ የተደራጁ መሆን ይኖርባቸዋል። ማዕከላቱ ለጎልማሳ ተሳታፊዎች ቅርብ የሆኑ፣ ንጽህናቸው የተጠበቀ፣ ለመዝናኛና ስፖርት እንቅስቃሴ አመቺ የሆኑና ለአዕምሮ ሰላም በመስጠት የሚስቡ መሆን አልባቸው።የመማማሪያአመሠራረት ከአገራችን ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ የሚነሳ ሆኖየሚከተሉትን መሰረታዊ ሀሳቦች ቀደም ብሎ ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡-

ሀ. የአካባቢውን ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ

ለ. የማህበረሰብ አገልግሎቶች

ሐ. ማህበራዊ መረጃ

መ. ኢኮኖሚያዊ መረጃ

የማኅበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የአካባቢዉ ኅብረተሰብ የስልጠና ማዕከላት (resource centers) ሆነዉ የሚያገለግሉ እንደመሆናቸዉ መጠን ሁሉም የአካባቢውማኅበረሰብ አባላት ማዕከላቱን በጋራ በማቋቋምና በማስተዳደር ለጋራ ጥቅም በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ ስለሆነም በአግባቡ የተደራጁ የማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት (CLC) ለኅብረተሰቡ የሚከተሉትን መሠረታዊ አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡

1. በራስ የመማማር (Self learning) የሚያበረታታ፣እራስን ለማብቃት የሚያስችል፣ የአካባቢዉ ማህበረሰብ በነጻነት እንደየተሳታፊዉ ፍጥነት ፍላጎቱን መሠረት ያደረገ የእድሜ ልክ ትምህርት የሚያገኝበት፣ ማህበረሰቡ ላጋጠመዉ ችግር ሀሳብን በመጋራት የጋራ መፍትሔ በመፈለግ በጋራ የሚያቅዱበት፣ የሚተገብሩበትና ዉጤቱንም በጋራ የሚጠቀሙበት፣ ባህላቸዉንና ሌሎች እሴቶቻቸዉን የሚያስቀጥሉበት ሆኖ ያገለግላል፡፡
2. የአካባቢዉ ማኅበረሰብ እንደየተግባራቸውአዳዲስ የልማት ሀሳቦችን የሚቀስሙበት፣ ያገኙትንም ልምድ በመተግበራቸው ለአጠቃላይ የተሻለ ለዉጥ የሚደግፋቸውና በተጨማሪም ራሳቸውን በሁሉም ዘርፎች ብቁ በማድረግ አቅሙ የጎለበተ ማህበረሰብ እንዲሆኑ ማስቻሉአብይ የሆኑት አገልግሎቶቹ ናቸው፡፡

### 1.8.1 የመማማሪያ ማዕከላቱ ቤትና ቦታ

የማኅበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት በመሆን ማገልገል የሚችሉ ተቋማት የሚከተሉት ሲሆኑ አመራረጣቸውም እንደአካባቢው ሁኔታ ይወሳናል።

**Formatted:** Indent: Left: 0.5", No bullets numbering

- ትምህርት ቤቶች
- በአካባቢዉ ማኅበረሰብ የተሰሩ ለተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መማማሪያ ጣቢያ የነበሩና ወደ ማኅበረሰብ መማማሪያ ማዕከልነት በማጎልበት የሚሸጋገሩና በቀጥታ ለማኅበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ታስበው የተሠሩ ቤቶች
- የገበሬዎች ማሠልጠኛ ማእከላት
- ተንቀሳቃሽ ትምህርት ቤቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የመማማሪያ ማዕከላቱ የሚኖራቸው የክፍል ብዛትና ስፋት ከአሉት ተሳታፊ ጎልማሶች ቁጥርና ከሚሰጠው የአገልግሎት ዓይነት ጋር እየተነፃጸረ የሚያድግ ሲሆን የሚሠሩትም ቤቶች እንደአካባቢው ማኅበረሰብ የኢኮኖሚ አቅም ይወሰናል። በተጨማሪምበተቻለ መጠን ቅጥር ግቢውም  ለተሳታፊ ጎልማሶች የስፖርትና መዝነኛ እንቅስቃሴዎችና የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን ማከናወኛ የሚሆን ተመጣጣኝ ስፋት ያለው ባዶ ቦታ ከመማማሪያ ማዕከላቱ ጋር እንዲኖሩ ቢደረግ ለፕሮግራሙ ውጤታማ አፈፃጸም ትልቅ አቅም ይፈጥራል።

### 1.8.2 የሰዉ ኃይል

የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ውስጥ ቅጥር አመቻቾችን በመጠቀም ማሰራት ተገቢ ነው፡፡ ከማዕከሉ የሚገኘው ጥቅም እየጎላ ሲመጣና በማዕከሉ የሚሰጡ ትምህርትና ስልጠናዎች ቁጥር እየጨመረ በሚመጣበት ወቅት በዚያዉ ልክ በመስኩ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ወደ ማዕከሉ ማምጣት የግድ የሚል ነው፡፡ በመሆኑም በማኅበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ውስጥ በመስኩ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በቋሚነት መቅጠርና መጠቀም ተገቢ ነዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመደበኛ ት/ቤት አስተማሪዎችን ፣የግብርና የጤና ኤክስቴንሺን ሰራኞችን የሌሎች ተቋማት ባለሙያዎችንና በጎ ፈቃኞች  ወ.ዘ.ተ በአመቻችነት መጠቀም አስፈላጊ ነዉ፡፡

### 1.8.3 የቁሳቁስና ሀብት ምደባ

በማኅበረሰብ መማማሪያሊኖሩ የሚገባቸው ቁሳቁሶች  የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ  ናቸው፡፡

- ወንበርና ጠረጴዛ ፣
- ጥቁር ሰሌዳ፣ የመጽሀፍ መደርደሪያዎችና ካቢኔቶች፣
- ንጹህ የመጠጥ ዉሃ በአካባቢው በቅርብ መገኘቱንና መብራት በመማማሪያ ማዕከላቱ መግበቱን
- ሌሎች የመማማሪያ ቁሳቁሶች፣ ለምሳሌ,ጋዜጦች፣ መጽሔት፣ መፅሀፍት፣ የሳታላይት ዲስክ፣ ኮምፒውተር፣ ፕላዝማ፤ ቴሌቪዥን፣ ቪዲዮ፣ ራዲዮ ሴት፣  ቴፕ ሪኮርደር፣ ስዕላዊ መጽሐፍት፣ ጌሞች፣ የአካል ብቃት መሳሪያዎች፣ ቻርቶች፣ ፓምፕሌቶች፣ የማስታወሻ ደብተር፣ የማስታወቂያ ሰሌዳ፣ የአካባቢ ካርታዎች ለምሳሌ፤ ት/ቤቶችን፣ የመንግስት ተቋማትን፣ ታሪካዊ ቦታዎችን፣ የቱሪስት መስዕቦችን፣ ተራራና ኮረብታዎች፣ ወንዞችን፣

ግድቦችን፣ የጤና ኬላዎችን፣ ሆስፒታሎችን ወዘተ የሚያሳዩ በመማማሪያ ማዕከሉ ዉስጥ ሊኖሩ  የሚገባቸው ናቸው፡፡

## 1.9 በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የሚሰጡ አገልግሎቶች/ ፕሮግራሞች

1. በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ዉስጥ የተለያዩ አገልግሎቶች ለተሳታፊ ጎልማሶች የሚሰጡ ሲሆን የሚከተሉት  በዋናነት ይጠቀሳሉ፡-**የሙያ ክህሎት ፡-** ሰዎች የሙያ ክህሎታቸዉን ከተለያየ አቅጣጫ ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ አገር በቀል ጥበብ/እዉቀት፣ የካበተ ልምድ ካላቸዉ ሰዎች፣ ከአሰልጣኞችና ከተለያየ መገናኛ ብዙሀን ወይንም ከማህበረሰቡ ሊማሩና ዕውቀትና ክህሎትን ሊጨብጡና ሊያዳብሩ ይችላሉ፡፡  ይህ የሙያ ማሻሻያ ክህሎት የራሳቸዉንና የቤተሰቦቻቸውን ገቢ ከማሳደግም ባሻገር የአገር ኢኮኖሚንም ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለዉ፡፡ ስለሆነም በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ውስጥ ከላይ በተጠቀሱት ነጥቦች አማካኝነት ተሳታፊ ጎልማሶች ሊማማሩ ይችላሉ፡፡
2. **መረጃ  ማግኘት** (Information service)**፡-**  የትኛዉም ማህበረሰብ በፈለገ ጊዜ በዕድሜ ዘመኑ ሁሉ ትምህርትና ስልጠና የማግኘት መብት አለው፡፡ ይህ ማለት ተሳታፊዎች በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከል ዉስጥ በቤተ መጽሐፍት ማንበብ ሲችሉ፣ በተለያዩ ቦታዎች የተሰሩ አኩሪ ስራዎች በኤግዚብሽን መልክ ቀርበው ማየት ሲችሉ፣ በራዲዮ ፕሮግራም፣ በሳተላይት ቴሌቪዥን፣ ወይንም በኢንተርኔት መጠቀም ሲችሉ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በማዕከሉ የሚገኙ ተሳታፊ ወጣቶችና ጎልማሶች መረጃን በማግኘት ዕውቀትና ክህሎታቸውን ለማዳበር ያስችላቸዋል፡፡
3. **የመዝናኛ ማዕከል** (Recreation) ፡-  ጎልማሶች በህይወት ዘመናቸው ያካበቷቸውን የተለያዩ ተሞክሮዎች፣ የጋራ ባህልና ወግ ልማዳቸውን ለሌሎች ለማካፈል እንዲሁም የአካል ብቃታቸውን ለማሳደግ በተለያዩ የመዝናኛ መስኮች ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ጎልማሶች በማህበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ውስጥ ሊያገኙዋቸውና ልምድ ሊለዋወጡባቸው ከሚገቡ መዝናኛዎች መካከል የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡-
   - ❖ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ፣
   - ❖ የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮች፣
   - ❖ ድራማ፣ ዳንስና ሌሎች ባህላዊና ዘመናዊ የሙዚቃ ጨዋታዎች፣
   - ❖ ስነ-ስዕል፣

- ❖ የተለያዩ የራዲዮ ፕሮግራሞች፣ የሳተላይት ቴሌቪዥን፣ ወይንም ኢንተርኔት በመጠቀም መዝናናትና ዕውቀት መገብየት ሲሆኑ ሁሉም ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች ዋነኛ አላማቸው የአካባቢውን የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከል( CLC) ተሳታፊዎች አንድነት ማጠናከርና በመግባባት እና መረጃ በመለዋወጥ ላይ የተመሰረተ የአኗኗር ዘይቤ እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡

4. **የጤና አጠባበቅ** (Health & Hygiene):- ይህ አይነቱ ፕሮግራም ተሳታፊዎች የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላትን በመጠቀም በሽታን ስለ መከላከል፣ መሰረታዊ የግልና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ እንዲሁም የተመጣጠነ ምግብ አመጋገብና ሌሎች ጤና ነክ የሆኑ ትምህርትና ስልጠናዎችን የሚያገኙበት ነው፡፡ ስለሆነም ተሳታፊዎች የግልና የቤተሰቦቻቸውን ጤና ለመጠበቅ፣ ጤናማ የሆነ አመጋገብ እንዲኖራቸውና የአካባቢያቸውን ንጽህና እንዲጠብቁ ለማስቻል ይህ ፕሮግራም በማዕከሉ ውስጥ ይሰጣል፡፡

**የኑሮ ደረጃን ማሻሻል** (Quality of Life Improvement):- የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከል በሚገኝበት አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አዛውንቶችና አካል ጉዳተኞች ወዘተ ተደራጅተው የዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከታቸውን በማሳደግ ኑሮአቸውን ማሻሻል ይችላሉ፡፡ በዚህ መሰረት ተሳተፊ ጎልማሶች በመማማሪያ ማዕከሉ በመገኘት በራስ አገዝ ትምህርትና በጋራ ውይይት የተለያዩ ትምህርቶችና አጫጭር ስልጠናዎችን በማግኘት የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን የኑሮ ሁኔታ በማሻሻል የአገራችንን እድገት ለማፋጠን ያግዛል፡6.

**አጫጭር ስልጠናዎች፡-**

በማህበረሰብመማማሪያማዕከላትዉስጥየሚሰጡአጫጭርሥልጠናዎችንበአራትክፍለንልናያቸዉእን ችላለን፡፡እነሱም፡-

- ❖ ሁለገብ ክህሎት (Generic skills)፡- የሚባሉት ተሳታፊ ጎልማሶች በመማማሪያ ማዕከሉ ውስጥ በጋራ በመወያየት የጋራ ችግሮቻቸውን መፍታት የሚችሉበትና እና ስራቸውን በጋራ ውይይት የሚሰሩበት ክህሎት ማለት ነዉ፡፡
- ❖ አካባቢያዊ ክህሎት (Contextual Skills):- ይህ ማለት ከተሳታፊዎች የእለት ተእለት የኑሮ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ክህሎት የሚያገኙበት ለምሳሌ ፡-ከጤና ፣ከግብርና፣ ከቤተሰብ የአኗኗር ሁኔታ፣ እንዲሁም ከጠቅላላ አካባቢያዊ ግንዛቤ ጋር የተያያዘ ክህሎት የሚገኝበት ማለት ነዉ፡፡

- ውህድ ክህሎት (Composition skills):- የሚባለዉ ሁለገብ ክህሎትና አካባቢያዊ ክህሎትን ከማንበብ፣ መጻፍና መስላት ክህሎት ጋር ተጣምሮ የሚገኝ ክህሎት ማለት ነዉ፡፡

ልዩ ልዩ የሙያ ክህሎት (Miscellaneous skill):- የምንለዉ ተሳታፊ ጎልማሶች በማእከል ዉስጥ ስለ ምግብ ዝግጅት፣ ጸጉር ማስተካከልና የመሳሰሉ ክህሎቶችን ለማግኘት አጫጭርስልጠናዎችንየሚያገኙበትነው፡፡**1.10የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት(CLC) ተሳታፊዎች/ ተጠቃሚዎች**

በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት በአካባቢው የሚገኙ ማኅበረሳብ አባላት ተጣቃሚ/ተሰታፊ ይሆናሉ፡፡

- ከመደበኛው አንደኛ ደረጃ ትምህርት የመጀመሪያ ሳይክል በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርታቸውን ያቋረጡ ወጣቶችና ጎልማሶች፣
- በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ላይ በመከታታል ላይ ያሉና ያጠናቀቁ ጎልማሶች፣
- በድህር የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም በመከታተል ላይ ያሉና ያጠናቀቁ ጎልማሶች፣
- ለችግር ተጋላጭ (Vulnerable) የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች፡-
    - የሴተኛ አዳሪዎች
    - የጎዳና ተዳዳሪዎች
    - የህግ ታራሚዎች
    - ተፈናቃዮችና ስደተኞች
- በጠረፍና ገጠራማ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ/ የኑሮ ዘይቤያቸው ለመደበኛ ትምህርት መከታተል የማያስችላቸው፤-
    - አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች
    - አሳ አስጋሪዎች
- ልዩ ፍላጎት የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች
- የከተማ ዋሪዎች፡
    - በአነስተኛ ገቢ የሚተዳደሩ
    - የቤት እመቤቶች
    - የቤት ሰራተኞች
    - የፋብረካ ሰራተኞች

- የቀን ሰራተኞች
- አካል ጉዳተኞች ይሆናሉ፡፡

## 1.11. የማህበረሰብ መማማሪያማዕከላትአደረጃጀትና አመራር

የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከል የህብረተሰቡ የትምህርትና የስልጠና ማዕከል ሲሆኑ የአካባቢውን ማህበረሰብ ክፍሎች በጋራ በማወያየትና በማሳተፍ የሚደራጁና የሚመሩ ናቸው።

የመማማሪያ ማዕከሉ ራሱን ችሎ እንዲቆም ለማድረግ የአካባቢው ህብረተሰቡ በባለቤትነት ማዕከላቱን በራሳቸው ማስተዳደር እንዳለባቸው የተለያዩ ሀገራት ተሞክሮ ያስረዳሉ ፡፡ ነገርግን አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በአካባቢው ማህበረሰብ መሉ ለመሉ በባለቤትነት እንዲያስተዳድሩ ማድረግ ስለማይቻል በየደረጃው የሚገኙ የቦርድ አባል መስሪያቤቶች ለማህበረሰቡ የግንዘቤ ማስጨበጫ ስልጠና በመስጠትና የማዕከላቱን የተግበራ እንቅስቃሴ በመከታተል ቀስ በቀስ ማህበረሰቡን ተሳታፊነትና ባለቤትነት በማሳደግ ማህበረሰቡ እንዲመሩት የማድረግ ስራ በሰፊው መስራት ይጠይቃል ፡፡ ስለሆነም ከፌደራል የጎልማሶች የቦርድ አባል መስራያ ቤቶች ጀምሮ ያሉ የቦድር አባል መስሪያቤቶች ተግባርና ኣላፊነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1.11.1 የፌደራል ቦርድ አባላት ተግባርና ሃላፊነት

የጎልማሶች ትምህርትን በቦርድ አባልነት እየመሩ ያሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሴክተር መስሪያ ቤቶችን የሚወክሉ የከፍተኛ አመራር አካላት ሲሆኑ ተግባርና ሃላፊነታቸውም እንደሚከተለው ተቀምጧል፡-

- የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ስለሚስፋፉበት ሁኔታ ስልቶችን ይቀይሳል፣
- የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ጥራትና ብቃት ለማስጠበቅ አስፈላጊውን ቴክኒክና ሙያዊ ድጋፍ ለክልል ቦርድ አባል መስራያ ቤቶች ይሰጣል፣
- የመማማሪያ ማዕከላቱ የልማት ፖሊሲዎች የሚተገበርባቸው የስልጠና ማዕከል በመሆን ስለሚያገለግሉ የአጫጭር ስልጠና መስጫ ማዕከላት እንዲሆኑ በየሴክተራቸው ግንዛቤ እንዲፈጠር ያደረጋሉ፡፡
- በየሴክተራቸው የሚከናወኑትን የልማት ፕሮግራሞች የማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላትን የአጫጭር የስልጠና መስጫ ማዕከላት በማድረግ እንዲገለገሉባቸው አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

- ለማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ማደራጃ የሚሆን በጀት እንዲመደብ ያደርጋል፣ ከለጋሽ ድርጅቶችም ሀብት ያፈላልጋል፣
- የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ጠንካራ የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣
- በየክልሉ/ ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የቦርድ አባል መስሪያቤቶችን የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት አፈፃፀማቸውን ይደግፋል፤ ይከታተላል፣ በመገምገም ግብረመልስ ይሰጣል፣
- የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የትምህርትና ስልጠና መሥጫ ማዕከላት ስለሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ሌሎች ባለድርሻ አካላት  በጥራት እንዲተገብሩ ያበረታታል፣ በመካከላቸው ጠንካራ አጋርነት እንዲኖር ያደርጋል፣
- በማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላት ዙሪያ ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ ያበረታታል፣
- በየሴክተሩ የሚዘጋጁ  የልማት ጹሁፎች  በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ተደራጅተው እንድቀመጡና የአካባቢው ማህበረሰብ እንዲቀምጥባቸው ያደርጋል፣
- እንደ አስፈላጊነቱ  የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ባለሙያዎች ስለማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላት ምንነት፣ አደረጃጀትና አመራር በተመለከተ ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ልምድ የሚለዋወጡበትን መድረኮች ያመቻቻል፣ በክልል ደረጃ ለሚካሂዱ ስልጠናዎች እንደ አስፈላጊነቱ ድጋፍ ያደረጋል፣
- የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ለማስፋፋት የሚያግዙ ፕሮክጀቶችን ዝግጅት ያሰተባብራል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣
- ቦርዱ በየሩብ ዓመቱ ግንኙነት በማድረግ ስራዎችን የገመግማል ግብረመልስ ይሰጣል

### 1.12.2 የፌደራል ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ተግባርና ሃላፊነት

የቴክኒክ ኮሚቴዎች ከቦርድ አባል መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ ሲሆን በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት አደረጃጀት፣ አመራርና አተገባበር ላይ የቴክኒካል እገዛ የሚያደርጉ ሃላፊዎች ወይም ባለሙያዎች ሲሆኑ ተግባርና ሃላፊነታቸው እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

- ለማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የሚሆኑ የተለያዩ ማስፈጸሚያ ሰነዶችን በጋራ በመሆን ያዘጋጃል፡፡

- የሴክተር መስሪያ ቤቶች ፕሮግራሙን በቅንጅት ለመፈጸም የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በጋራ ያዘጋጃል፣
- በማህበረስብ መማማሪያ ማዕከላት የሚሰጡ ወቅታዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ጽሁፎችን ያዘጋጃሉ፣ ለክልሎች እንዲሰራጭ ክትትል ያደርጋል፣
- በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የሚካተቱ ፕሮግራሞችን የፍላጎት ጥናት በማድረግ ይለያል፣
- በመስክ በመገኘት በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ላይ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፣
- በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ዙሪያ በየደረጃው የአህዝቦት ስራዎች እንዲሰሩና ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እንዲካሄድ ያደርጋል፣
- የቴክኒክ ኮሚቴው ቢያንስ በየሩብ አመቱ በመገናኘት ስራን በጋራ ይገመግማሉ፣ የግምገማውን ውጤቱም ለቦርዱ ያቀርባል፣

### 1.12.3 የክልል/የከተማ አስተዳደር ቦርድ አባላት ተግባርና ሃላፊነት

በክልልና ከተማ አስተደሮችም ቦርዱ በማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላት አጠቃቀም ላይ ራሱን የቻለ ተግባርና ሀላፊነት የሚኖረው ሲሆን ይህም እንደሚከተለው ተቀምጧል፡-

- በማህበረሰብ መማማሪ ማዕከላት ዙሪያ በፌደራል ደረጃ የተዘጋጁ የማስፈጸሚያ መመሪያዎች ክልላዊና ከተማአቀፍ ይዘት እንዲኖራቸው ያደርጋል፣
- የመማማሪያ ማዕከላቱ የልማት ፖሊሲዎች የሚተገበርባቸው የስልጠና ማዕከል በመሆን ስለሚያገለግሉ የአጫጭር ስልጠና መስጫ ማዕከላት እንዲሆኑ በየሴክተራቸው ግንዛቤ እንዲፈጠር ያደረጋል፡፡
- በየሴክተራቸው የሚከናወኑትን የልማት ፕሮግራሞች የማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላትን የአጫጭር የስልጠና መስጫ ማዕከላት በማድረግ እንዲገለገሉባቸው አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
- በክልሉ ስር በሚገኙ ዞኖችና ወረዳዎች በማህበረሰብ መማማሪያ መዕከላት ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትልና ዕገዛ ያደርጋል፣
- ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ የሚሆን ሀብት ይመድባል፣
- በክልሉ ውስጥ የሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላት የሚሰጡ አገልግሎቶች ዙሪያ ላይ ገብተው እንዲሰሩ ያበረታታል፣

- በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ላይ እየተሳተፉ ያሉ ጎልማሶችን መረጃ ተጠናቅረው እንዲያዙ ክትትል ያደርጋል፣
- በማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላት ዙሪያ በክልል ደረጃ ጥናትና ምርምር ዕንዲካሄድ ያግዛል፣ ይደግፋል፣
- ምርጥ ተሞክሮ ካላቸው የክልል/የከተማ አስተዳደሮች የልምድ ልውውጥ እንደካሄድ ስርዓት ይዘረጋል፣
- በዞንና በወረዳ ለሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተሰማሩባቸው የልማት ዘርፎች የማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላትን እንደግባት በመጠቀም የልማት ስራ ማከናወኛ ተቋም ማድረግ እንዲሁም እነዚህንም ማዕከላት በግባት እንዲሚሉ ያስተባብራል፣ ይከታተላል
- ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣

### 1.12.4 የክልል/ የከተማ አስተዳደር ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ተግባርና ሃላፊነት

- የክልል የቴክኒክ ኮሚቴዎች ከቦርድ አባል መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ ሲሆን በማኅበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት አደረጃጀት፣አመራርና ትግባራ ላይ ሙያዊ እገዛ የሚያደርጉ ሃላፊዎች ወይም ባለሙያዎች ናቸው፡፡ የክልል/የከተማ አስተዳደር ቴክኒክ ኮሚቴዎች ተጠሪነታቸው ለክልል ቦርድ ይሆናል፣

ተግባርና ኃላፊነታቸውም እንደሚከተለው ተቀምጧል፡-

- በክልሉ/የከተማ አስተዳደር በማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላት የሚከናወኑ ተግባራት ዕቅድ ያዘጋጃሉ፣
- በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ውስጥ በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት እየተሳተፉ የሚገኙ ጎልማሶችን መረጃ ይሰበስባሉ፣ ያጠናቅራሉ፣
- ስለ ማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ምንነት፣ አደረጃጀትና አመራር ለወረዳና ለዞን ቴክኒክ ኮሜቴ አባላት የቴክኒክና የሙያ ዕገዛ ያደረጋል፣
- በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች እንዲካሄዱ ድጋፎችን ያደርጋል፣
- በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ትግበራ ላይ ጥናትና ምርምር ያደርጋል፣
- ለማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የተለያዩ ግብአቶች መሟላታቸውን ክትትል ያደርጋል፣ ለቦርዱም ያሳውቃል፣

❖ የቴክኒክ ኮሚቴው ቢያንስ በየሁለት ወሩ እየተገናኘ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት አፈፃጸም ይገመግማል፣ ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል፣

❖ በየሩብ ዓመቱ ግንኙነት በማድረግ ስራዎችን የገመግማል ግብረመልስ ይሰጣል

### 1.12.5 የዞን/ ወረዳ ቦርድ አባላት ተግባርና ሃላፊነት

ከላይ በክልል ደረጃ በተቀመጠው መሰረት በዞን/ወረዳ ደረጃ ያለው ቦርድም የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት በበላይነት ይመራል፡፡ በመሆኑም የዞኑ/ወረዳው ቦርድ ተግባርና ሃላፊነት እንደሚከተለው ተቀምጧል፡-

❖ የማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላት እንዲደራጁና የተግባር እንቅስቃሴ እንዲያከናውኑ በጀት ይመድባል በግባትም እንዲሚሉ ያደርጋል፣

❖ በወረዳ/ዞን ደረጃ በማህበረሰብ መማማሪ ማእከላት የሚተገበሩ ግቦችን ይወስናል፣

❖ በወረዳው/በዞኑ ውስጥ ባሉ ቀበሌዎች ያለውን የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላትን ትግበራ ሂደት በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

❖ የመማማሪያ ማዕከላቱ የልማት ፖሊሲዎች የሚተገበርባቸው የስልጠና ማዕከል በመሆን ስለሚያገለግሉ የአጫጭር ስልጠና መስጫ ማዕከላት እንዲሆኑ በየሴክተራቸው ግንዛቤ እንዲፈጠር ያደረጋል፡፡

❖ በየሴክተራቸው የሚከናወኑትን የልማት ፕሮግራሞች የማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላትን የአጫጭር የስልጠና መስጫ ማዕከላት በማድረግ እንዲገለገሉባቸው አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

❖ በወረዳው/ዞኑ የሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የሙያ ድጋፍ እንዲያደረጉ ያስተባብራል፣

❖ በክልል ደረጃ የማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላት በተመለከተ የተዘጋጁ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋል፣

❖ በማህበረሰብ መማማሪ ማእከላት ተሳታፊዎችና በሚከናወኑ ተግባራት መረጃ ከቀበሌዎች በመሰብሰብ በየደረጃው ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ደርጋል፣

❖ በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት በየሩብ ዓመቱ አንድ ጊዜ በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

❖ በየወሩ በመገኛነት ተግባራትን ይገመግማል ግብረመልስ ይሰጣል

❖ በማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላት የሚሰጡ ይዘቶች ዙሪያ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል፣

ረቂቅ

### 1.12.6 የዞን/ ወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ተግባርና ሃላፊነት

የቴክኒክ ኮሚቴው በዞን/በወረዳው ከሚገኙ የቦርድ አባላት ውስጥ የተውጣጡ ባለሙያዎች ያካተተ ሲሆን ተጠሪነቱ ለወረዳው/ዞኑ ቦርድ አባላት ይሆናል፣ተግባርና ሃላፊነቱም እንደሚከተለው ይሆናል፡-

- 
- የቴክኒክ ኮሚቴው በወረዳው የማህበረሰብ መመማሪያ ማዕከላት ለሚከናወኑት ተግባራት  ዕቅድ ያቅዳል፣
- ሁሉንም የልማት አጀንዳዎች በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት አቀናጅቶ ለመተግባር የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ ያደርጋል፣
- በወረዳው በሚገኙ የማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላት  የተለያዩ አገልግሎቶችን ማኅበረሰቡ እንዲያገኝ ያደርጋል፣
- በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የተሳታፊዎችን ፍላጎት መሠረት ያደረገ ፕሮግራሞችን ለማቅረብ  የአካባቢ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል፣
- በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ምንነት፣ ፋይዳ፣ አደረጃጀትና አመራር ላይ የአህዝቦት ስራዎች እንዲካሄዱ ያስተባብራል፣
- በየሳምንቱ  በመገናኘት ስራን ይገመግማል፣ ወቅታዊ መረጃም ወደ ሚመለከትው አካል ያቀርባል፣

በተዘረጋው የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መሠረት በቀበሌዎች  በወር አንድ ጊዜ በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ያካሂዳል፣

### 1.12.7 የቀበሌ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ ተግባርና ሀላፊነት

ከላይ በወረዳ ደረጃ በተቀመጠው መሠረት በቀበሌ ደረጃ ያለው ቦርድም የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት     በበላይነት ይመራል፡፡ በመሆኑም የቀበሌው ቦርድ ተግባርና ሃላፊነት እንደሚከተለው ተቀምጧል፡-

- የማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላትን ያደራጃል በጀት መመደቡንና ግብዓት መሟላቱን ይከታተላል፣
- በቀበሌው የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የመከናወኑትን ተግባራት አመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ያጸድቃል እንዲሁም ይተገብራል፣
- በቀበሌ ደረጃ በማህበረሰብ መማማሪ ማእከላት የሚተገበሩ ግቦችን ይወስናል፣

- በቀበሌ ደረጃ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላትን የትግበራ ሂደት በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣
- ስለ ማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ምንነት፣ ፋይዳ፣ አተገባበር፣ ባለቤትነትና ቀጣይነት ለአካባቢው ማህበረሰብ ግንዛቤ ያስጨብጣል፣
- በቀበሌው የሚከናወኑትን የልማት ፕሮግራሞች የማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላትን የአጫጭር የስልጠና መስጫ ማዕከላት በማድረግ እንዲገለገሉባቸው ያደርጋል፣
- በቀበሌው የሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ባለሀብቶች ለማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የሙያ ድጋፍ እንዲያደረጉ ያስተባብራል፣
- የማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላትን በተመለከተ የተዘጋጁ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋል፣
- በማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላትን የሚመለከቱ መረጃዎችን በመያዝና በማደራጀት ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ደርጋል፣
- ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶችን በየወሩ ለሚመለከተው ቦርድ ይልካል
- በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት በሳምንት አንድ ጊዜ በመገኘት ክትትልና ድጋፍ እንዲደረግ ያግዛል፣
- በማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላት የሚሰጡ ይዘቶች ዙሪያ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ስካሄድ ድጋፍ ይሰጣል፣
- ህብረተሰቡ ስለመማማሪያ ማዕከላቱ ግንባታና ለሌሎች ተግባራት በገንዘብና ቁሳቁስ እንዲያግዙ ያበረታታል፣
- አመቻቾች እንዲቀጠሩና ከግብርናና ጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች እንዲሁም ሌሎች ጋር በቅንጅት እንዲሰሩ ያስተባብራል፣
- ከሌላ አካባቢ ከሚገኝ የመማማሪያ ማእከል ጋር ልምድ በመለዋወጥ ተሞክሮን ያስፋፋሉ፣
- በመማማሪያ ማዕከላቱ የሚከናወኑት ተግባራት የተሳታፊዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ ክትትል ያደርጋል፣

በየቀበሌው የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ የማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላትን ተግባራዊ ለማድረግ በቦርዱ ሰብሰቢነት የሚመራ የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ኮሜቴ እንዲቋቋም ያደርጋል፡፡ የኮሚቴው አባላትም ከተለያዩ የአካባቢው ማህበረሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ይሆናሉ፡፡ እነሱም በአካባቢው የሚገኙ መምህራን፣ በጡረታ የተገለሉ

ሙህራን፣ የሀይማኖት መሪዎች ፣ ታዋቂ ሽማግሌዎች፣ ባለሀብቶች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ የጎልማሶች ትምህርት ጣቢያ ኃላፊ፣ አመቻቾች፣ የሴቶችና የወጣቶች ተወካዮች ወዘተ…. የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ኮሚቴውም ከቀበሌው ቦርድ ጋር በመሆንና ቦርዱ በሚሰጣቸው ኃላፊነት መሠረት ተግባራትን ያከናወናሉ።

### 1.12.8. የመማማ ማኔጅመንት ኮሚቴተግባርና ሃለፊነት

- የማህበረሰቡን ፍላጎት መዳሰስና መለየት በእቅድ እንዲታቀፍ ማድረግ
- አሳታፊና በተግባር ሊተገበር የሚችል እቅድ በቴክኒክ ኮሚቴ የቀረበውን ተመልክቶ ማጽደቅ
- የማዕከሉን አጠቃላይ ስራዎችን በበላይነት ማስተባበር፡ ማቀናጀት፡ መምራት፡ ማስተዳደር፡ ወዘተ
- የሀብትና ግብአት ምንጮችን ለይቶ መሰብሰብ ገቢ ማድረግ
- አመቻቾችና የሙያ አሰልጣኞችን መቅጠርና ማሰማራት
- ሕብረተሰቡን በአስፈላጊ ወቅታዊ አጀንዳዎች ላይ ማወያየት
- የበጎ አድራጎትና ፈቃደኞችን ማፈላለግና ማስተባበር
- ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ ሀሳቦችን ማሳየት
- ጠቃሚ እስትራቴጂዎችን በመንደፍ ስራ ላይ ማዋል
- ስለ የማመማ እንቅስቃሴን የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ማስተዋወቅቀጣይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

### 1.12.8 **የማህበረሰቡ ተግባርና ኃላፊነት**

- የመማማሪያ ማእከሉን በመምራትና በማስተዳደር ይሳተፋሉ ፣
- የማዕከሉን ቀጣይነት ለማረጋገጥ በገንዘብ፣ በእውቀት፣ በቁሳቁስና በጉልበት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡
- በማዕከሉ ይገለገላሉ
  ከፍላጎት ዳሰሳ ጥናት እስከ ክትትልና ግምገማ በንቃት ይሳተፋሉ

### **1.13በማህበረሰብ ተሳትፎ፣ ባለቤትነትናየማህበረሰብ መማማሪ ማእከላትቀጣይነትን ማረጋገጥ፣**

በማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የማህበረሰቡ ተሳትፎ እና ባለቤትነት በእጅጉ የተቆራኙ ጉዳዮች ናቸዉ፡፡ በብዙዎቹ አገሮች የማህበረሰብ መማማሪያ ማእከላት ስኬቶች በማህበረሰቡ ተሳትፎና ባለቤትነት ደረጃ ይለካል፡፡ ይኸዉም የአንድ

ፕሮግራም ቀጣይነት የሚረጋገጠዉ ማህበረሰቡ በፕሮግራሙ በምልአትና በያገባኛል ስሜት /በቆራጥነት ሲሳተፍ ነዉ፡፡

በማህበረሰብ ተሳትፎ፣ በባለቤትነትና በማእከሉ ቀጣይነት መካከል ጠንካራ ቁርኝት አላቸዉ፡፡ ምክንያቱም ማህበረሰቡ ይበልጥ በተሳትፈ ቁጥር ይበልጥ ባለቤትነት ይሰማዋል፣ ይህም ፕሮግራሙን ይበልጥ ቀጣይ ስለሚያደርገዉ ነዉ፡፡ ይህ ተጠይቃዊነት (Logical) ያለዉ ቁርኝት መሆኑን የብዙ አገሮች ልምድ ያስረዳል፡፡

ተሳትፎ ለባለቤትነት መጎልበት ወሳኝ የመሆኑን ያህል የባለቤትነት ስሜት መጎልበት በበኩሉ ለቀጣይነት መረጋገጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡የማህበረሰብ አባላት ተሳትፎ የሚገለፀዉ በስመ ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን በማዕከላቱ አስተዳደር፣ አመራርና እቅድ ዝግጅት እንዲሁም በዉሳኔ ሰጪነት ማህበረሰቡ በንቃት በመሳተፍ ነዉ፡፡

በአንዳንድ አገሮች ተሞክሮ መሠረት ለማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት ቀጣይነት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት፡-

- ማዕከላቱ ለማህበረሰቡ በሚሰጡት ጠቀሜታ መጠን (ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሰጡ ከሆነ ዘላቂነቱ አስተማማኝ ይሆናል)
- የማዕከላቱ ራስን በራስ የመቻልና አስፈረላጊ ፋሲሊቲዎችን የማሟላ አቅም እና
- የማዕከላቱ አገልግሎቶች የማህበረሰቡን የትምህርትና ሥልጠና ፍላጎቶች የሚያሟሉ መሆን ናቸዉ፡፡

ቀጣይነት የሚጎለብተዉና ከጊዜ ወደ ጊዜ ዘላቂ እየሆነ የሚሄደዉ ለማህበረሰቡ አባላት እዉቅና በመስጠት በትልቅ አክብሮት ስንቀበላቸዉ፣ እንዲሁም ተሳትፎአቸዉን በተለያየ መልኩ ስናበረታታ ነዉ፡፡ የማእከላቱ የአስተዳደርና የትግበራ ብቃት ባደገ ቁጥር የማህበረሰቡ ባለቤትነትና ቀጣይነት ይበልጥ እየጎለበተ ይሄዳል፡፡

በአጠቃላይ የማህበረሰብ ተሳትፎንና ባለቤትነትን በማጎልበት ቀጣይነትን ለማረጋገጥ፣

- የፕሮግራሙን እቅድና ትግበራን አሳታፊ ማድረግ፣
- ማህበረሰቡ የራሱን ልማት የመቆጣጠር፣የቅድሚያ ፍላጎቱን ራሱ ለይቶ እንዲወስንና ለችግሮቹ የራሱን መፍትሔዎች እንዲሰጥ ማበረታታት፣
- ማህበረሰቡ ለፕሮግራሙ የአቅሙን ያህል የቁሳቁስ፣ የገንዘብና የጉልበት አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ፣

- ❖ ከማህበረሰቡ የተዉጣጡ አባላትን ያቀፈ የማኔጅመንት ኮሚቴ ማቋቋምና ለኮሚቴዉ አባላት በፕሮግራሙ አመራር፣ አስተዳደር፣ እቅድ ዝግጅትና በመሳሰሉት ላይ ስልጠና በመስጠት አቅማቸዉን መገንባትና ለፕሮግራሙ ቀጣይነት የበኩላቸዉን ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል፣
- ❖ የተለያዩ የግንዛቤ ማሳደጊያ መድረኮችን በመጠቀም በህብረተሰቡ ዘንድ ተከታታይ ቅስቀሳ ማካሄድ ናቸዉ፡፡

## 1.14 ለማህበረሰቡ መማማሪያ ማዕከላት የሚሆን ሀብት መመደብና ማሰባሰብ

### 1.14.1 ከመንግስት ለማዕከላቱ የሚመደብ በጀት

መንግሥት በ2017ዓ.ም. አገራችን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን በማደረግ ላይ እንደሚገኝ ይተወቃል፡፡ ይህም ሽግግር ከከፍተኛ ቴክኖሎጂ አቅም የሚመነጭ የግብርና ምርታመነት እድገት በኢንዱስትሪው የሚመራ ኢኮኖሚ የመገንባት አቅጣጫ መከተል እንደሚያስፈልገት በሂደቱም ያለፉ ሌሎች ሀገሮች ተሞክሮዎች ያሣያል፡፡

ከዚህ አንፃር በምርት ላይ ቀጥተኛ ተሳተፊ የሆነው ጎልማሳው የህብረተሰብት ክፍለ በማስተማርና በማሰልጠን አቅሙን ለማጎልት የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የማህበረሰብ መማማሪያ መእከላት የጎላ ሚና ይጫወታሉ፡፡

በመሆኑም የእነዚህን የመማሪያ መእከላት ግብ ለማሳካት የህገሪቱ አቅም የፈቀደውን ያህል በቂ በጀት መመደብ ወሳኝ ስለሆነ በማእከላቱ የሚሰጡት የትምህርትና የስልጣና አገልግሎቶች የጥራት ደረጃቸውን በጠበቀ ሁኔታ እንዲሰጡ ለማድረግ መንግሥት በጀት መመደብ አስፈላጊ ነው፡፡

### 1.14.2 ከተለያዮ ለጋሽ  አካላት የሚገኝ ድጋፍ፤-

ከመንግሥት ከሚመደበው በጀት በተጨማሪ የማእከላቱን ግቦች ስኬታማ ለማድረግ ከተለያዩ ምንጮች መለትም ከኅብረተሰብ፤ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅትች፤ ከግለሰቦች የግል ድርጅቶች፤  ከሲቪል ማህበራት፤ ከባለሃብቶችና ከመሳሰሉት ተገቢውን ሀብት ማሰባሳብና መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

### 1.14.3 የሀብት ማሳባሰቢያ ዘዴዎች፡-

- ❖ ኅብረተሰቡን በማሰተፍ እንዲለግስ ማድርግ
- ❖ ከለጋሽና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አሰተዋፅኦ እንዲያደርጉ ማድረግ

- ገንዘብ ለማሰባሰብ የተለያዩ የተለያዩ የገቢ ማስገኛ መድርኮችን ማዘጋጀት
- የተለያዩ ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም ለምሳሌ ማዕከላቱ የራሳቸው ገቢ
- እንዲያመነጩ ማድረግ

## 1.15 የማህበረሰብ መማማሪያ ማዕከል ክትትልና ግምገማ

### 1.15.1 የክትትልና ግምገማ ዓላማ

- በማእከሉ ትግበራ ሂደት ያጋጠሙ ክፍተቶችንና ድክመቶችን በመለየት ድጋፍ ለመስጠት፣
- በክትትልና ደግፍ የተገኙ አበረታች ውጤቶችንና ጠንካራ ጎኖችን በመለየት እንዲጎለብቱ በማድረግ የልምድ ለውውጥ የሚደረግባቸውን ስልቶች ለመቀየስ፣
- ማዕከላቱ በተጠቃሚ በማኅበረሰቡ ኑሮ ላይ ያመጠውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦችን ለመለየትና አጠናክሮ ለማስቀጠል፣
- የተጠናከረ የመረጃ አያያዝና ፍሰት ሥርዓት መኖሩን ለማረጋገጥና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠት፣
- በማእከላቱ ግልፅነትና የተጠያቂነት ያለው አሰራርን ለማስፈን፡፡

### 1.15.2 የክትትልና ግምገማ ሚና

- ክትትልና ግምገማ በአንድ ትምህርታዊ ፕሮግራም አተገባበር ሂደት ዉሥጥ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ተግባር ነው፡፡ በተለይ ግምገማ የአንድ ፕሮግራም ዋነኛ አካል ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን ዋና ተግባሩም የመማማሪያ ማእከሉ የሚገጥሙትን ችግሮች ለመለየት፣ የተከሰቱትን የግብዓት አጥረቶች በማወቅ ዉሳኔ በመስጠት የማእከሉን አፈጻጸም ለማሻሻል ብሎም የፕሮግራሙ አላማዎች ግብ በመምታት ለመለካት ዋነኛ መሳሪያ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ክትትልና ግምገማ የመማማሪያ ማእከል ሥርዓተ ትምህርት እና የተዘጋጁት የትምህርት መሳሪያዎች የተዘጋጁበትን ዓላማ በብቃት ለማሟላት ይችሉ ዘንድ መከለስና መለወጥ የሚያስፈልጋቸዉ መሆን አለመሆናቸዉን ለመወሰን ይጠቅማል፡፡

### 1.15.3 በክትትልና ግምገማ ሂደት ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች

- ለማእከሉ የሚውለው ገንዘብ ከየት እንደተገኘና ገንዘቡ በአቅዱ መሰረት በአግባቡ ስለመዋሉ፣
- ለማእከሉ ማስፈጸሚያ በቂ የሆነ ሀብት ስለመኖሩ፣

- ❖ ከማእከሉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያገኙ የሚችሉ የልማት ሴክተሮች የትኞቹ እንደሆኑ፣
- ❖ በማእከሉ የሚሰጡ የትምህርትና የስልጠና ይዘቶች ተገቢነት፣
- ❖ የመማማሪያና የስልጠና መሣሪያዎች የተሳታፊዎችን የይዘት ምርጫና ፍላጎት የሚያሟሉ ስለመሆኑ፣
- ❖ በማእከሉ የተለያዩ የባለድረሻ አካለትና የልማት መስሪያ ቤቶች ተሳትፎና ቅንጅታዊ አሰራር ስለመኖሩ ፣
- ❖ የመማማሪያ ማእከሉ በአጠቃላይ በአገር ኢኮኖሚ ላይ ስለሚያሳድረዉ አንድምታ
- ❖ ማእከሉ የድህነት አዙሪትን ለመስበርና የተሳታፊዉን ኑሮ ለማሻሻል ስለሚያበረክተው አስተዋጽኦ፣
- ❖ ማእከሉ ለአገር ገጽታ ግንባታ አስተዋጽኦ ስለማበርከቱ፣
- ❖ ማእከሉ በህብረተሰቡ ሕይወት ላይ ስለሚያመጣዉ ተጨባጭ ለዉጥ፣

## 1.16 ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸው ጉዳዮች

- ❖ የማህበረሰብ መማማሪያ መእከላትን ወደ ተግባር ሊያስገቡ የሚችሉ የመግባቢያ ሰነዶችን በየደረጃው መፈራረምና መእከላቱን በየአካባቢው ማቋቋም
- ❖ የማዕከላቱ ምንነት፣ፋይዳና የአተገባበር ሂደቱን አስመልክቶ በየደረጃው ለሚገኙየመንግስት አካላት፣ ፈፃሚዎችና ለህብረተሰቡ ተከታታይ የትውውቅና የግንዛቤ ማሳደጊያ መድርክ መፍጠር
- ❖ በማእከላቱ የተፈለገውን አገልግሎት በብቃትና በጥራት ለመስጠት የሚያስችሉ የመማማሪያና ማሳልጠኛ ማሳሪያዎችና ሌሎች ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎችን ማሟላት
- ❖ የማዕከላቱን ሥራ የሚሰራና የሚያስተባብር በቂ የሰው ሃይል በየማዕከላቱ መመደብ
- ❖ መልካም ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥና ለመተግበር የሚያስችል የግንኙነት መረብ (Network) መንሥግታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከሲቪክ ማህበራት ጋር መመስረት

በቀጣይ በዚህ መመሪያ መነሻነት ለማኅበረሰብ መማማሪያ ማዕከላት የጥራት ማስጠበቂያ ዝርዝር ስታንደርድ ማዘጋጀት።

ረቂቅ ጽሑፍ